**ቀን:-16/11/2002**

**የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ም/ቤቶች አፈ-ጉባኤዎች**
**በስዊዘርላንድ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጋር በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ተወያዩ::**

የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈ-ጉባኤ ክቡር አምባሳደር ተሾመ ቶጋና የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ-ጉባኤ አቶ ደግፌ ቡላ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በስዊዘርላንድ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ጋር ውይይት አካሄዱ:: ውይይቱ የተካሄደው በኢፌዲ.ሪ የጄኔቭ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት አዘጋጅነት ሐምሌ 15/2002 ዓ.ም. ነበር::

ውይይቱ በምርጫ 2002፤ በቀጣይ የአምስት ዓመት የመንግስት ዕቅዶችና በዲያስፖራውና በመንግስት መካከል ስላለው ግንኙነት ላይ አተኩሮ የተካሄደ ነበር:: አፈ-ጉባኤ ተሾመ ኢሕአዴግ ለ2002 ምርጫ ዝግጅት የጀመረው በ1997 ምርጫ የታዩትን ድክመቶች በመገምገም እንደነበር፤ በዚህም የዲሞክራሲ ተቋማትን ማጠናከርና የዲሞክራሲ ባህልን ማሣደግ አስፈላጊ መሆናቸውን ተገንዝቦ በርካታ ተግባራትን ማከናወኑን አብራርተዋል::

የዲሞክራሲ ተቋማትን ለማጠናከር መንግስት በርካታ የሕግ መሻሻያዎችን ማድረጉን አፈ-ጉባኤው ተናግረው፤ በዚህ ረገድ የምርጫ ቦርድ በአዲስ መልክ የተደራጀ ሲሆን፤ በዚህም ቦርዱ የነበረውን አሣታፊነት እንዲያሳድግና የመወዳደሪያ ሜዳውም ለሁሉም ፓርቲዎች እኩል እንዲሆን ተደርጓል:: የቦርድ አባላት አሰያየም የተቃዋሚ ፓርቲዎች የተሣተፉበት ሲሆን፤ በዚህም አሁን ካሉት የቦርድ አባላት አራቱ በተቃዋሚዎች የተጠቆሙ ናቸው:: የምርጫ ቦርድን የአፈጻጸም አቅም ለማሣደግ የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል::

አፈ-ጉባኤው በማያያዝም እንዳብራሩት የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት፤ የፌዴሬሽን ም/ቤትና የክልል ም/ቤቶችን ዲሞክራሲያዊነትና አሣታፊነት የሚያጎለብቱ በርካታ ማሻሻያዎች ተተግብረዋል:: የሚድያ፤ የሲቪል ማህበረሰብና የፀረ ሽብርተኝነት ህጎችም መውጣታቸውን አፈ-ጉባኤው ገልጸው፤ ሕጎቹ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን የሚያጎለብቱ እንደሆኑ አስረድተዋል:: የፍትህ ስርዓቱንና የሲቪል ሰርቪሱን ውጤታማነት የሚያሳድጉ በርካታ ተግባራት መከናወናቸው አስታውሰዋል::

የዲሞክራሲ ባህል ለማጎልበትም የ1997 ምርጫ ተከትሎ ከህዝቡ ጋር ተከታታይ ውይይቶች መደረጋቸውና የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራዊ ጉዳዮች ላይ በጋራ የሚመካከሩበት መድረክም መፈጠሩን አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ገልጸዋል::

ገዢው ፓርቲ በኢኮኖሚና ማህበራዊ መስኮችም አበረታች ውጤቶችን ማስመዝገቡን ያስታወሱት አፈ-ጉባኤው፤ ከምርጫ 97 ተገቢውን ትምህርት የቀሰመው ኢህአዴግ በምርጫ 2002 ሶስት ዓላማዎችን ይዞ መንቀሳቀሱን አብራርተዋል:: ዓላማዎቹም ምርጫውን ሠላማዊ፤ ዲሞክራሲያዊ፤ ነጻና ፍትሃዊ ማድረግ፤ ምርጫውን ተዓማኒነት እንዲኖረው

ማስቻልና በምርጫው ማሸነፍ ነበሩ:: በምርጫ 2002 ዓላማዎቹን በሙሉ ማሣካቱን የጠቆሙት አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ዋናው ጉዳይ ሕዝቡ በከፍተኛ ቁጥር በመውጣት በነጻነት፣ በዲሞክራሲያዊና በፍላጎቱ የሚፈልገውን መምረጥ መቻሉ መሆኑን አስምረውበታል:: ይህም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከምርጫ 97 ወዲህ የሕዝብ ተሣትፎ አይኖረውም የሚለውን አባባል ውድቅ ያደረገ ነው ብለዋል::

አፈ-ጉባኤ ተሾመ ኢህአዴግ በቀጣይ 5 ዓመታት መንግስት የሚኖረውን ዕቅድ እየገመገመ መሆኑን አመልክተው፣ መንግስት በቀጣይ 5 ዓመት በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መሠረታዊ ሽግግር (transformation) እንዲኖር በማተኮር እንደሚሠራና፣ ለዚህም በመመዝገብ ላይ ያለውን የጥምር አሀዝ የኢኮኖሚ ዕድገት አጠናክሮ የማስቀጠል አስፈላጊነት ዋነኛ መሆኑን፣ ባለፉት ዓመታት በኢኮኖሚው የታዩትን የዋጋ ንረትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት በቀጣይነት መቅረፍ እንደሚተኮርበት ገልጸው፣ በዚህም መንግስት የምዕተ ዓመቱን ግቦች ለማሣካት እንደሚሠራ ተናግረዋል::

የመሠረተ ልማት ግንባታ እንደሚቀጥልና በቀጣዩ አምስት ዓመታትም አገሪቱን በአራቱም ማዕዘን የሚያገናኝ የባቡር ሃዲድ ለመግባት ዕቅድ መያዙን፣ የትምህርት ጥራት የመንግስት ትኩረት እንደሆነና በጤና ዘርፍ የምዕተ ዓመቱን ግቦች ለማሣካት እንደሚሠራና፣ በቀጣይ 5 ዓመታት ተጨማሪ 10 ዩኒቨርስቲዎች እንደሚገቡ አፈ-ጉባኤው አብራርተዋል::

አፈ-ጉባኤ ተሾመ ቶጋ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሚና አስመልክቶ ባደረጉት ገለጻ የምርጫ 2002 ሂደትና ውጤት እንደ የኢትዮጵያ ህዝብ ድል መታየት እንዳለበት ጠቁመው፣ እነሱም በአገራቸው ልማት በተለያየ መልኩ ሊሣተፉ እንደሚገባ፣ በተለይም በኢንቨስትመንት እንዲሣተፉ ጥሪ አቅርበዋል:: ምሁራን ወገኖችም የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ እንዲሳተፉና በኢትዮጵያ ልማት ሁሉም ዜጋ ድርሻውን ሊያበረክት እንደሚገባ ተናግረዋል::

የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ አቶ ደግፌ ቡላ በበኩላቸው ምርጫ 2002 የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸነፈበት መሆኑን፣ የምርጫው ውጤት ሕዝቡ ከምርጫ 97 ወዲህ ያሉ ጉዳዮችን በመገምገም ትክክለኛ ውሣኔ ያስተላለፈበት ነው ብለዋል:: በዚህም ህዝቡ መንግስት ያስመዘገባቸውን የኢኮኖሚ ውጤቶችና ስህተቱን ማረሙን መገንዘቡን፣ በተቃራኒው ተቃዋሚዎች እርስ በርስ መከፋፈላቸውንና የመንግስትን ስልጣን ለመያዝ ብቃት እንደሌላቸው በሰጠው ውሣኔ ማሳየቱን አፈ-ጉባኤ ደግፌ ተናግረዋል::

በቀጣይ 5 ዓመታት መልካም አስተዳደር በማስፈን ረገድ በርካታ ስራዎች እንደሚሠሩ ገልጸው፣ በኢትዮጵያ እየተመዘገበ ያለው የልማት ውጤት፣ በልማት የተሣተፉ አካላት ሁሉ ድል በመሆኑ፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም በዚሁ እንዲሣተፍ ጠይቀዋል::

ተሣታፊዎቹም የተለያዩ ጥያቄዎችን በመሰንዘር የነቃ ተሣትፎ አሣይተዋል:: ካነሱዋቸው ጥያቄዎች መካከል ቀጣዩ ፓርላማ ምን ይመስላል? ተቃዋመዎችን ተዓማኒ ለማድረግ መንግስት ምን አቅዷል? በምርጫው ለማሸነፍ መራጮችን አዋክቧችኋል ይባላልና ምላሻችሁ ምንድን ነው? መንግስት ሙስናን ለመዋጋት ቁርጠኝነት አለው ወይ? ከጎረቤት አገሮች ጋር ያለን ግንኙነት በተለይም በአባይ የተነሣ ከግብጽ ጋር ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል? ስለ ወደብ መንግስት ምን አቋም አለው? ጥምር ዜግነት ለምን አይፈቀድም? የሚሉ ይገኙበታል::

ለተነሡት ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡት አፈ-ጉባኤ ተሾመ ቀጣዩ ፓርላማ ዋነኛ ኃላፊነቱ የሆነውን የህግ ማውጣት ስራ እንደሚቀጥል፣ ቀድሞውንም ቢሆን አብላጫ ድምጽ ያገኘው ድርጅት ህግ በአብላጫ ድምጽ እንደሚያጽድቅ፣ በቀጣዩ ፓርላማ የኢህአዴግ ም/ቤት አባላት በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችን በማንሣት አስፈጻሚውን አካል ሊከራከሩ እንደሚችሉ፣ ተቃዋሚዎችም በአገራዊ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ እንደሚደረግ፣ ለዚህም ለአብነት መገናኛ

ብዙሃንን መጠቀም እንደሚችሉ፣ ከሕዝቡም ጋር በነጻነት እንዲሰሩ ሕገ-መንግስቱ እንደሚፈቅድ፣ ሆኖም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከመንግስት ጋር በጋራ ጉዳዮች ላይ አብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው ገልጸዋል።

ኢህአዴግ በ2002 ምርጫ ማንንም እንዳላስገደደ፣ 1997 ምርጫ ትምህርት በመውሠዱ ጠቃሚ የሆነ የልማት ስራ እንኳ የሚሰራው ቀድሞ በማወያየት እንደሆነ፣ ምርጫው በነጻነት የተካሄደ እንደነበረ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚመሠክረው እንደሆነ ተገልጿል።

መንግስት ሙስናን ለመዋጋት ቁርጠኛ መሆኑን የገለጹት አፈ-ጉባኤ ተሾመ፣ ለዚህም ተቋም ማቋቋሙን በመግለጽ በቀጣይም ሙስናን የመዋጋቱ ትግል ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመልክተዋል።

ከጎረቤት አገሮች ጋር ስላለው ግንኙነት በሚመለከት ለተነሣው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ከሱዳን፣ ከጂቡቲ፣ ከኬንያ፣ ጋር ያለን ግንኙነት በጣም ጥሩ እንደሆነ፣ የሶማሊያን የውስጥ ቀውስ ለመፍታት መንግስት እየሠራ እንደሆነ፣ ሆኖም የሶማሊያ ችግር በዋነኝነት የሚፈታው በሶማሊያውያን በራሳቸው እንደሆነ፣ ከኤርትራ ጋር ሠላማዊ ግንኙነት እንዲኖር ለማድረግ መንግስት በየትኛውም ጊዜና ቦታ ለድርድር ዝግጁ እንደሆነ፣ ሆኖም እስካሁን በኤርትራ በኩል የሰላም አጋር የሆነ መንግስት እንዳላገኘ፣ መንግስት ዋነኛ ትኩረት የተጀመረው የሰላምና የዲሞክራሲያያዊ የልማት ጎዳና እንዳይደናቀፉ እንደሆነ፣ ይህንንም ለማስጠበቅ ዝግጁነት እንዳለው ተሠምሮበታል። ወደቡን በሚመለከት መንግስት አማራጭ ወደቦችን ለማበራከት እንደሚሠራ ተብራርቷል።

ግብጽን በሚመለከት፣ ከግብጽ ጋር ያለው ግንኙነት ታሪካዊ መሆኑን፣ ሆኖም ኢትዮጵያን እስከመኖሯ የዘነጋውን እ.ኤ.አ. በ1929 እና በ1959 በቅኝ ገዢዎች የተፈረመውንና የናይልን ወንዝ ከግብጽና ሱዳን ጥቅም ብቻ እንዲውል የሚፈቅደውን ስምምነት ኢትዮጵያ እንደማትቀበለውና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ሁሉም አገሮች የናይልን ወንዝ በልማት የሚያውሉበትን አዲስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት እንደፈረመች፣ ይህም ግብጽን ጨምሮ ሁሉንም የናይል ተፋሰስ አገሮች ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑን ገልጸዋል። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያውያን የግብጽ አቋም ፍትሃዊ አለመሆኑን፣ የኢትዮጵያና የላይኛው ተፋሰስ አገሮችም በወንዙ የመጠቀም ሉአላዊ መብት እንዳላቸውና ይህም የግብጽን የመጠቀም መብት እንደማይጻረር በማስረዳት የዜግነት ግዴታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል። የጥምር ዜግነትን በተመለከተ ሕገ-መንግስቱ እንደማይፈቅድ፣ ሆኖም ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከውጭ ጉዳይ፣ መከላከያና ደኅንነትና ከፋይናንስ መስኮች ውጪ እንደ ኢትዮጵያውያን የሚታዩበት ህግ መኖሩንና ይህ ለኢንቨስትመንት አመቺ ሁኔታ እንደሚፈጥር ገልጸዋል።